## የህይወት ጓደኛዎ ወንጀለኛ ሆኖ ከተገኘሳ?

የኑሮ ጓደኛዎ በፈጸመው የዶመስቲክ ቫዮለንስ ወንጀል ወንጀለኛ ሆኖ ከተገኘ፣ ምክር እንዲያገኝ፣ በፕሮቤሽን ወይም በፓሮል ኦፊሰር ክትትል እንዲደረግለትና አስፈላጊ ከሆነም እስር ሊፈረድበት ይችላል። ፍርድ ቤቱ፣ ለእርስዎ ደህንነት ሲል ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ የግንኙነት መከላከያ ትእዛዝ (No Contact Order) ሊያስተላልፍ ይችላል።

## ደህንነቴን ለመጠበቅ ሌላ ምን ማድረግ እችላለሁ?

የመከላከያ ትእዛዝ (Order for Protection) ለማግኘት ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ይህ ዓይነት ትእዛዝ፣ የህይወት ጓደኛዎ ቤትዎ እንዳይገባ የሚከለክል፣ እርስዎን እንዳያስጨንቅና ከእርስዎ ጋር እንዳይገናኝ የሚከለክል፣ ልጆችዎን ከዋሺንግተን ሲቴት እንዳያስወጣ የሚከለክለውና ጊዚያዊ የጉብኝት የጊዜ ሰንጠረዥ እንዲዘጋጅ የሚያዝ ትእዛዝ ነው። የመከላከያ ትእዛዝ (Order for Protection) ለማግኘት አሜሪካዊ ዜጋ መሆን ወይም ግሪን ካርድ እንዲኖርዎ አያስፈልግም። ለንደዚህ ዓይነት ትእዛዝ በአቅራቢያዎ በሚገኝ ፍርድ ቤት ውስጥ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ልዩ ጠበቃ ይረድዎታል።

በማሕበራዊ የአገልግሎት ምንጮች (Community Resources) ሥር ከተዘረዘሩት ኤጀንሲዎች፣ ከአንዱ ጋር መገናኘት ይችላሉ። እነዚህ ኤጀንሲዎች የግል ናቸው። ስለሆነም የመንግስት አካል አይደሉም። ጠበቃ፣ ከደህንነትዎን የሚጠብቅ እቅድ ሲያወጡና ልብስ፣ ምግብ፣ መጠለያና እርዳታ በመፈለግ ሊተባበርዎ ይችላል።

በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ከሚገባውና ሊረዳዎ ከሚችል፣ እርስዎ ከሚያምኑት ሰው ጋር መነጋገር ይችላሉ።

ከታች ከተዘረዘሩት ኤጀንሲዎች ጋር በመገናኘት፣ ስላልዎ ሕጋዊ መብቶች መማርና ሕግ ነክ እርዳታ ማግኘት ይችላሉ።

## ማሕበራዊ የአገልግሎት ምንጮች (Community Resources)

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ኤጀንሲዎች ሁሉ የግል ናቸው። ስለሆነም፣ የመንግስት ወይም የ INS አካል አይደሉም።

- **Abused Deaf Women's Advocacy Services**
  (ለTDD ብቻ)
  206-236-3134
- **Asian/Pacific Islander Women & Family Safety Center**
  206-467-9976
- **Chaya (ለደቡብ እስያ ሴቶች)**
  206-325-0325
- **Consejo Counseling & Referral Service**
  206-461-4880
- **Domestic Abuse Women's Network (DAWN)**
  425-656-7867
- **Eastside Domestic Violence Program**
  425-746-1940 ይም1-800-827-8840
- **Jewish Family Service**
  206-461-3240
- **New Beginnings**
  206-522-9472
- **Northwest Network for Bisexual, Trans, & Lesbian Survivors of Abuse**
  206-568-7777፣ 206-517-9670
- **Refugee Women's Alliance (ለ14 ቋንቋ ተናጋሪ ሕብረተሰቦች አገልግሎት ይሰጣል)**
  206-721-0243
- **Seattle Indian Health Board**
  206-324-9360፣ ኤክስቴንሽን 802
- **YWCA**
  206-568-7845 ይም 425-226-1266

## ሕግ ነክ የአገልግሎት ምንጮች(Legal Resources)

- **CLEAR** (የተቀናበረ ሕግ ነክ ትምሕርት ምክርና አመራር ሲስተም (Coordinated Legal Education Advice and Referral System)፤ ለሲቪላዊ ሕጋዊ ጉዳዮች እርዳታ ለማግኘት የሚያገለግል በነጻ የሚሰራ የስልክ አገልግሎት።
  888-201-1014፣ TTY 1-888-201-9737
- **Northwest Immigrants Rights Project,**
  206-587-4009 ይም 800-445-5771
- **Northwest Justice Project**
  206-464-1519፣www.nwjustice.org
- **Northwest Women's Law Center**
  206-621-7691

ይህ ፕሮጀክት፣ ለሲያትል ከተማ ፍርድ ቤት፣ ከViolence Against Women Grants Office፣ Office of Justice Programs, U.S. Department of Justice በተሰጠው እርዳታ ቁጥር 2001-WF-BX-003፣ ነው እርዳታ ያገኘው። በዚህ ሰንድ ላይ ያሉ ሐሳቦች ሁሉ የጸሐፊው ናቸው። ስለሆነም የ Department of Justice አቋም ወይም ፖሊሲዎችን አይወክሉም።

AMHARIC

BE\81613 MUNI COURT-MULTI LANGUAGE STOP DOMESTIC VIOLENCE FLYER\AMHARIC.P65 rev. 12/17/02

# በቤትዎ ውስጥ ማንኛውም ሰው ጉዳት እያደረሰብዎ ካለ

# የሚከላከሉልዎት ሕጎች አሉ።

ለሲያትልና ኪንግ ካውንቲ፣ WA የሚያገለግል መረጃ

## ዶመስቲክ ቫዮለንስ ምንድነው?

የኑሮ ጓደኛዎ (ባለቤትዎ፣ የወንድ ጓደኛዎ ወይም "የድሮ ጓደኛዎ") ይቀናብዎታል ወይ? ከጓደኞዎችዎና ቤተሰብዎ ጋር እንዳይገናኙ ይከለክልዎታል ወይ? ሥራ እንዳያገኙ ይከለክልዎታል ወይ? ልጆችዎን እንደሚነጥቅዎ ዝቶብዎት ያውቃል ወይ? ሪፖርት ሊያስደርግዎ ዝቶብዎት ያውቃል ወይ?

የህይወት ጓደኛዎ፣ አካላዊ ጉዳት አድርሶብዎት ያውቃል ወይ? ይህም ሲባል፣ በጥፊ መምታትን፣ መግፋትን፣ በቡጢ መምታትን፣ በዘብጣ መማታትን፣ ማነቅን ወይም ጸጉርዎን መሳብን ያጠቃልላል። እንደ ሽጉጥ፣ ቢላዋ ወይም ሌሎች እቃዎች በመሳሰሉ መሳሪያዎች፣ ጉዳት እንደሚያደርስብዎ ዝቶብዎት ያውቃል ወይ? ብጥብጡ የተነሳው በእርስዎ ምክንያት እንደሆነ ይነግርዎታል ወይ?

ከዚህ በላይ ለተጠየቁት ጥያቄዎች አዎ ብለው መልስ ከሰጡ፣ በሚያጎሳቁል ግንኙነት ውስጥ ነው መኖር የያዙት። አደጋም ሊደርስብዎ ይችላል። ብቻዎን አይደሉም። ሌሎች ብዙ ሰዎች በንደዚህ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከተዘረዘሩት ኤጀንሲዎች ጋር በመገናኘት እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ፣ አሰቃዩን "እሱ" ብለን የወንድ ቅጽል-ስም ሰጥተነዋል። ነገር ግን፣ ማንኛውም ሰው፣ ወንድም ይሁን ሴት በሽሪኩ ጉስቁልና ሊደርስበት ይችላል።

## ዶመስቲክ ቫዮለንስ ሕገወጥ ነው ወይ?

በዙ የዶመስቲክ ቫዮለንስ አይነቶች በዋሺንግተን ስቴት ሕገወጥ ናቸው። ባለቤትዎ ወይም የህይወት ጓደኛዎ፣ በማንኛውም መንገድ አካላዊ ጉዳት ማድረስ፣ እርስዎ ሳይፈልጉ፣ በግድ የግብረ ስጋ ግን ኑነት ከእርሱ ጋር እንዲፈጽሙ ማስገደድ፣ እርስዎን ወይም ልጆችዎን እንደሚጎዳ ወይም እንደሚገድል ወይም ንብረትዎን እንደሚያወድም መዛት ሕገወጥ ነው። በዶመስቲክ ቫዮለንስ ምክንያት ጉዳት ከደረሰብዎ፣ የሚካላከሉልዎ ሕጎች አሉ።

## ፖሊስ መጥራት አለብኝ ወይ?

አደጋ ላይ ካሉ፣ 9-1-1 በመደወል ከፖሊስ እርዳታ ያግኙ። ትክክለኛውን የጎዳና አድራሻ፣ ምን እንደተፈጸመ፣ መቼ እንደተፈጸመ፣ የሽሪክዎን ስም፣ የተወለደበትን ቀን፣ የመኪና ታርጋ ቁጥርና አካላዊ መግለጫ (የጸጉር ቀለም፣ የቆዳ ቀለም፣ እድሜ፣ ቁመት፣ ሚዛን) በትክክል እንዲሰጡ ይጠየቃሉ። ኦፐሬተሩ ፖሊሶችን ወደ ቤትዎ ይልካል። እቤትዎ እስኪደርሱ ድረስ መጠበቅ ይኖርብዎታል ማለት ነው። የሚፈሩ ከሆኑ፣ ኦፐሬተሩ የስልክ መስመሩን ሳይዘጋ እንዲቆይ ሊጠይቁት ይችላሉ።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ የማይናገሩ ከሆኑ፣ ኦፐሬተሩን ምን አይነት ቋንቋ እንደሚናገሩ (በእንግሊዝኛ) ይንገሩት። የ911 ኦፐሬተሩ የእርስዎን ቋንቋ ከሚናገር (በ AT&T የስልክ መስመር አድርጎ) ሰው ጋር በስልክ ያገናኝዎታል። ከዛ በኋላ ከሁለት ሰዎች ጋር ይነጋገራሉ፣ ይህም ሲባል፣ ከአስተርጓሚውና ከ911 ኦፐሬተሩ ጋር ማለት ነው።

## ፖሊስ በቦታው ከደርሰ በኋላ ምን ይፈጸማል?

ፖሊስ በቤትዎ ከደረሰ በኋላ፣ እርስዎንና የኑሮ ጓደኛዎ በመለያየት፣ የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጥይቅዎታል። ስለ ፍጻሜው አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ ለመስጠት ይሞክሩ። ጉዳት ከደረሰብዎ፣ ያልዎትን ሰንበሮች፣ ምልክቶች፣ የቆሰለ የአካል ክፍል ወይም ሌሎች ጉዳቶችን፣ ለፖሊሱ ያሳዩት። የኑሮ ጓደኛዎ፣ ከዚህ በፊት፣ ጉዳት አድርሶብዎ ከሆነ ወይም ዝቶብዎ ከሆነ፣ ለፖሊሱ ስለተፈጸመው ታሪክ በዝርዝር ይግለጹለት።

ለፖሊስ የመግለጽ መብት አልዎት። ልጅዎ፣ የኑሮ ጓደኛዎ ሌሎች የቤተሰብዎ አባሎች፣ ለእርስዎ እንደ አስተርጓሚ ማገልገል የለባቸውም። ፖሊሱ በስልክ የሚያስተረጉም ሰው ሊጠራልዎ ይችላል። በእርስዎ ላይ ምን እንደተፈጸመ በቋንቋዎ ሊጽፉና ፖሊሱ ከሪፖርቱ ጋር አብሮ እንዲያጠቃልለው ሊጠይቁት ይችላሉ። በመኖሪያ ቤትዎ ውስጥ ሽጉጦች ካሉ፣ የት እንደሚገኙ ለፖሊሱ ይንገሩት። የፍጻሜውን ቁጥር (incident number) እንዲሰጥዎ ይጠይቁትና፣ ቁጥሩን ይጻፉት።

የዶመስቲክ ቫዮለንስ ጉዳት ስለ ደረሰባቸው ሰዎች ለ Immigration and Naturalization Service ሪፖርት ማቅረብ፣ የአካባቢ ፖሊስ ኤጀንሲዎች ፖሊሲ አይደለም። ስለ ኢሚግሬሽን ወረቀትዎ ከተጠየቁ፣ ጥያቄውን መመለስ እንደማይፈልጉና ከጠበቃ ጋር መነጋገር እንደሚፈልጉ ለፖሊሱ ሊነግሩት ይችላሉ።

## ፖሊስ ከታሰረ ምን ይሆናል?

ወንጀል እንደተፈጸመ ካመኑበት፣ ፖሊሶቹ የኑሮ ጓደኛዎ ሊያስሩት ይችላሉ። ወደ እስር ቤት ከወሰዱት፣ በጥቂት ሰዓቶች ውስጥ ሊፈታ ይችላል ወይም በርከት ላሉ ቀኖች ወይም ከዛ በላይ ለሆነ ጊዜ ሊታሰር ይችላል። ከ VINE (በኪንግ ካውንቲ እስር ቤት ብቻ ነው ይህ አገልግሎት ያለው) ጋር ከተመዘገቡ፣ ከእስር ቤት ሲፈታ፣ በስልክ እንደተፈታ ሊነገርዎ ይቻላል። ይህ ሲስተም ፣ ኮምፒዩተራይዝት የሆነ የስልክ ሲስተም ነው። ለዚህ በነጻ የሚሰጠው አገልግሎት ለመመዝገብ፣ በስልክ ቁጥር 1-877-425-8463 ይደውሉ።

## ፖሊስ ከታሰረ በኋላ ምን ይሆናል?

የኑሮ ጓደኛዎ ከታሰረ፣ አቃቤ ሕጉ ክስ ሊመሰርትበት ይችላል። ክስ የመመስረት ወይም ያለመመስረት ሐላፊነት የእርስዎ አይደለም። ክሱን የመመስረት ወይም ያለመመስረት ስልጣን ያለው ዓቃቤ ሕጉ ነው።

በጀመሪያው የፍርድ ቤት ቀጠሮ ላይ፣ የኑሮ ጓደኛዎ ከእርስዎ ጋር እንዳይገናኝ የሚያዝ የግንኙነት መከልከያ ትእዛዝ ዳኛው ሊያስተላልፍ ይችላል። ከእርስዎ ጋር በአካል፣ በስልክ ወይም በፖስታ ከተገናኙ፣ 9-1-1 በመደወል እንደገና ሊያሳስሩት ይችላሉ።

የግንኙነት መከልከያው ትእዛዝ፣ አብዛ ውንኛጊዜ ልጆችዎን አያጠቃልልም። ስለ ልጆችዎ ደህንነት ወይም ስለ ጉብኝት ስምምነቶችዎ ስጋት ያደረብዎት ከሆነ፣ የመከላከያ ትእዛዝ እንዲተላለፍልዎት ማመልከቻ ማስገባት አለብዎት።

## ወደ ፍርድ ቤት መሄድ ቢኖርብኝስ?

በወንጀል ጉዳይ ላይ፣ ከአንድ በላይ የፍርድ ቤት ቀጠሮች ሊኖሩ ይችላሉ። የፍርድ ስነስርዓት የሚፈጸም ከሆነ፣ በስልክ ወይም በጽሑፍ በፍርድ ቤቱ እንዲገኙ ይነገርዎታል። በፍርድ ቤቱ እንዳይቀርቡ ለመከልከል እንደሚሞክር ማንኛውም ሰው ከዛተብዎ፣ ይህ ወንጀል ስለሆነ ለፖሊስ ማሳወቅ ይችላሉ።

የፍርድ ቤቱን ሒደት መከታተል እንዲችሉ ጠበቃ ከእርስዎ ጋር አብሮ ይሰራል። ጠበቃዎ እንዴት ከእርስዎ ጋር መገናኘት እንደሚችል አረጋግጠው ይወቁ። በፍርድ ቤቱ ውስጥ፣ አቃቤ ሕጉና የተከሳሹ ጠበቃ፣ ስለ ተፈጸመው የዶመስቲክ ቫዮለንስ፣ ጥያቄዎችን ሊጠይቅዎ ይችላሉ።

## ከአንድ በላይ ፍርድ ቤት አለ ወይ?

በኪንግ ካውንቲ ውስጥ የተለያዩ ፍርድ ቤቶች አሉ። ጠበቃዎ ስለ ፍርድ ቤቱ ሲስተም በደምብ አድርጎ ያስረዳዎታል። የአካባቢ ፍርድ ቤቶች (የመዘጋጃና የሰፈር ወይም ዲስትሪክት) አነስተኛ ወንጀሎችን (misdemeanor) ያዳምጣሉ። የኪንግ ካውንቲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከበድ ያሉ ወንጀሎችንና (felony) እንደ ፍቺና ልጆች በየትኛው ወላጅ አደራ ስር መሆን እንዳለባቸው መወሰንን የሚያጠቃልሉ ቤተሰብ ነክ ክሶችን ያዳምጣል። የመከላከያ ትእዛዞች (Orders for Protection) ከነዚህ ፍርድቤቶች ሁሉ ማገኘት ይቻላል።

እርስዎና የኑሮ ጓደኛዎ፣ የተለያዩ ክሶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ካላችሁ፣ በአንዱ ፍርድ ቤት ውስጥ ያለው ዳኛ ስላልዎ ሌሎች ጉዳዮች መረጃ ይኖረዋል ብለው አያስቡ። እያንዳንዱ ፍርድ ቤት እራሱን ችሎ ነው የሚሰራው። እንደ የመከላከያ ትእዛዞችን (Orders for Protection) ና ግንኙነት መከልከያ ትእዛዞችን (No Contact Orders) የመሳሰሉ አስፈላጊ ሕጋዊ ሰነዶችን ሁሉ በእያንዳንዱ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ይዘው መቅረብ ይኖርብዎታል። እንዲሁም ስላልዎት ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ለጠበቃዎ ማሳወቅ ይኖርብዎታል።